# ከ93.3% እስከ 96.9% የአዲስ አበባ ነዋሪ በመደመር ሰልፍ እንዳልተሳተፈ ተረጋገጠ



*ከህዳሴ ኢትዮጵያ፣*

*ሰኔ 30፣ 2010 ዓ.ም.*

## *በሰኔ 16፣ 2010 ዓ.ም. በተደረገው የምስጋናና የመደመር ሰልፍ ከ93.3% – 96.9% የሚሆን የአዲስ አበባ ነዋሪ እንዳልተሳተፈ ተረጋገጠ*

የጥናቱ መነሻ የአስተባባሪው ኮሚቴ መግለጫዎችና መረጃ ሲሆን፤ እሱም በዚች የምስጋናና የመደመር ቀን በመስቀል አደባባይ የተገኘው የሰው ብዛት 5 ሚሊዮን ነው የሚል፣ እንዲሁም የአዲስ አበባ ነዋሪ ግምት መነሻ 3 ሚልዮን እንደ መነሻነት በመውሰድ፤ የGoogle Earth Map እና የስፋት መለኪያዎችን በመጠቀም ምን ያክል ሰው እንደተሰበሰበ ለማወቅ ጥረት ተደርጓል፡፡ በማህበራዊ ሚድያ ይነሱ ከነበሩ ጥያቄዎች አንዱ የአዲስ አበባ ነዋሪ ብዛት ከ3 ሚልዮን አይበልጥም ግን ደግሞ በሰልፉ ላይ ተሳትፏል የተባሉት ሲታይ 5 ሚልዮን ነው ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል የሚል ሲሆን፣ የሰልፉ አስተባባሪ ኮሚቴዎች ምላሽ ከ60% በላይ ከአዲስ አበባ ዙርያ እና ከአጎራባች ከተሞች ነው የመጣው ተባለ፡፡

ይህ እንደ መነሻነት በመውሰድ ሰኔ 16፣ መስቀል አደባባይ የተሰበሰበው የመደመር፣ የፍቅር፣ የይቅርታ እንዲሁም የጠቅላይ ሚኒስተራችን ዶ/ር አብዪ የምስጋና ተሳታፊ 40% የአዲስ አበባ ነዋሪ 60% ደግሞ የአዲስ አበባ አከባቢና አጎራባች ከተሞች ነዋሪ ነው የሚል እሳቤ ተወስዷል፡፡ እንደ አስተባባሪው ኮሚቴ መረጃ መሰረት2 ሚሊዮን ወይም 60% (2ሚልዮን ሲካፈል ለ3ሚልዮን) የአዲስ አበባ ነዋሪ በሰልፉ የተሳተፈ ሲሆን የተቀረው 3 ሚልዮን ተሳታፊ ግን ከአዲስ አበባ ውጭ የመጣ እንደሆነ ያሳያል፡፡

ጥናቱ ማረጋገጥ የፈለገው “ግን በትክክል ከ4 – 5 ሚሊዮን ሰው ተገኝቷል ወይ?” የሚል ነበር፡፡

ሰልፈኛው ባንዴራም፣ መፈክሮችም ሌሎች ለሰልፉ ያሸበርቃሉ ያልዋቸው ቁሳቁሶች ይዞ በአንድ ካሬ ሜትር (1ሜ በ 1ሜ) ቦታ በአማካይ ከ4-5 ሰው ይቆማል ካልን (ይህ ማለት በአንዳንድ ቦታ ተጨናንቆ ከዛ በላይ ሲሆን በአንዳንድ ቦታ ተዝናንቶ ከዛ በታችዘርዘር ያለ ይሆናል የሚል ታሳቢ በመውሰድ ነው) ምክንያቱ በፎቶግራፉ (ስዕል 1) እንደሚታየው ወደ ስቴጁ አከባቢ የተጨናነቀ ሲሆን ወደ ኋላና ጫፍ አከባቢ ሳሳ ያለ ነው፡፡

የተሰበሰበው ብዛት በአይን ዕይታ የሚከተለው ፎቶግራፍ ነው የሚመስለው፡፡ ይህን ፎቶግራፍ በማየት ሁሉም የየራሱ ግምት ሊሰጥ ይችላል፡፡ በትክክለኛው ሳይንሳዊ መመዘኛ በመውሰድ ይህ በፎቶግራፉ የምናየው ማዕበል በስንት ካሬ ሜትር ነው ያረፈው? ብዛቱስ ስንት ይሆናል?የሚል የመመለስ ዓላማ ነው የያዘው፡፡

*ስዕል 1 በመስቀል አደባባይ በሰኔ 16፣ 2010 ዓ.ም. በተደረገው የምስጋናና የመደመር ሰልፍ ያሳያል፡፡*



ክቡራን አንባቢዎች ወደ ሚቀጥለው ፅሁፍ ከመሻገራቹ በፊት ይህን ፎቶግራፍ በማየት ግምታችሁን እንድታስቀምጡ እና ግምታችሁ ከዚህ ትንታኔ ውጤት በማነፃፀር ራሳችሁን በራሳችሁ እንድትገመግሙ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡



ከሀዳሴ ኢትዮጵያ hidaseethiopia@yahoo.com ወይም hidaseethiopiaa@gmail.com

## *የቦታው ስፋትና የህዝብ ብዛት ስሌት*

ይህ በGoogle Map ሲለካ በሁለት እይታ ከፍለን እንየው፡፡ እሱም በብሩህ ወይም አዎንታዊ አመለካከት ወይም Optimistic (ስዕል 3)እና በጠባብ ወይም አሉታዊ አመለካከት Pessimistic (ስዕል 2)መሰረት በማድረግ እንየው፡፡

## *ጠበብ ያለ ወይም Pessimistic ዕይታ*

በጣም ሳታጋንን ሳታሰፋ በመስቀል አደባባይላይ ብቻ ወይም እላይ ያለው ፎቶግራፍ ብቻ ታጥረህ በGoogle Map አጥሩን በማበጀት የቦታው ስፋት ሲለካ እንደሚከተለው ስዕል ይሆናል፡፡ እታች (ስዕል 2) የጎግል ማፐ በቀይ ቀለም የተከበበው ስዕል በጎግል መለኪያ ስሌት መሰረት ቁመቱ 0.51 ኪ.ሜ. የሚጠጋ ሲሆን ዙርያው 1,486 ሜ. ሆኖ ስፋቱ ደግሞ76,516 ካ.ሜ ነው፡፡

እዚህ ላይ ሊሰበሰብ የሚችል የሰው ብዛት ማለትም እላይ እንደ መነሻነት የተወሰደው በአንድ ካሬ ሜትር ቦታ በአማካይ ከ4-5 ሰው ይቆማል የሚል እሳቤ በመውሰድ ሲሰላ፡-

= 76,516 $m^2$ X (4 to 5) = (ከ306,064 እስከ 382,580 ሰው) ይዛል ማለት ነው፡፡ አጥብቦ በማየት በመስቀል አደባባይ የወጣው ጠቅላላ የሰው ብዛት ከ306 ሺ እስከ 383 ሺ ብቻ ነው ማለት ነው፡፡ ይህ አስተባባሪ ኮሚቴ ካለው 5 ሚልዮን ሲነፃፀር ፈፅሞ አይገናኝም፡፡ ስለዚህ አስተባባሪው ኮሚቴ Pessimistic አይደለም፡፡

ስዕል 2 መስቀል አደባባይ በሰኔ 16፣ 2010 ዓ.ም. የተደረገው ሰልፍ ቦታ ስፋቱና ዙርያው ያሳያልPessimistic፡፡





ከሀዳሴ ኢትዮጵያ hidaseethiopia@yahoo.com ወይም hidaseethiopiaa@gmail.com

## Optimistic ኦፕቲሚስቲክዕይታ

አዎንታዊ አመለካከት በመያዝ በጣም ሰፊ መሬት ከመሰቀል አደባባይ ውጭ ያለውም ግምት ውስጥ_ በማስገባት ሲታይ

ስዕል 3 መስቀል አደባባይ በሰኔ 16፣ 2010 ዓ.ም. የተደረገው ሰልፍ ቦታ ስፋቱና ዙርያው ያሳያልOptimistic



እላይ (ስዕል 3)በቀይ ቀለም የተከበበው ስዕል በጎግል መለኪያ ስሌት መሰረት ቁመቱ 1.2 ኪ.ሜ. የሚጠጋ ሲሆን ዙርያው 3,341 ሜ. ሆኖ ስፋቱ ደግሞ 134,887 ካ.ሜ ነው፡፡

እዚህ ላይ ሊሰበሰብ የሚችል የሰው ብዛት ማለትም እላይ እንደ መነሻነት የተወሰደው በአንድ ካሬ ሜትር ቦታ በአማካይ ከ4-5 ሰው ይቆማል የሚል እሳቤ በመውሰድ ሲሰላ፡-

ሊሰበሰብ የሚችል የሰው ብዛት

= 134,887 $m^2$ X (4 to 5) = (ከ539,548 እስከ 674,435 ሰው) ይዛል ማለት ነው፡፡

የዚህም ትርጉም አንድ ለሰልፉ ፖዘቲቭ አመለካከት ያለው አካል ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ሲያሰላው እዚህ መሰብሰብ የሚችል ብዛት ከ540 ሺ እስከ 675 ሺ ብቻ ነው ማለት ነው፡፡ ይህ አስተባባሪ ኮሚቴ ካለው 5 ሚልዮን ሲነፃፀር አሁንም ፈፅሞ አይገናኝም፡፡

ስለዚህ በሰኔ 16፣ 2010 ዓ.ም. በተደረገው የምስጋናና የመደመር ሰልፍ በአጠቃላይከ306 ሺ የማያንስ እንዲሁም ከ675 ሺ የማይበልጥ ሰው ነበር በመስቀል አደባባይ የተሰበሰበው፡፡

***<u>ከዚህ ስሌት መረዳት የሚቻለው</u>***

አሁንም የአስተባባሪው ኮሚቴ የአ.አ. እና የአከባቢው ሬሾ 40፡60 የሚለውን ወስዶ ሲታይ (60% ከአ.አ. ውጭ ሆኖ 40% ደግሞ የአ.አ. ነዋሪ)በመውሰድ በተጨባጭ በሰልፉ የተሳተፈው ሰው ብዛት

- የአዲስ አበባ ነዋሪ ሆኖ በሰኔ 16፣ 2010 ዓ.ም. በተደረገው የምስጋናና የመደመር ሰልፍ የተሳተፈውከ122.4 ሺ እስከ270 ሺ ቢቻ ሲሆን፣ ይህ ማለት ደግሞ የአዲስ አበባ ህዝብ ብዛት 3 ሚልዮን ከሆነ ***<u>ከ4.08%</u>***እስከ***<u>9.0% የአዲስ አበባ ነዋሪ</u>*** ስብሰባው ላይ ተገኝቷል ማለት ነው፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው የተቀረት91.00% – 95.92% የአዲስ አበባ ነዋሪ በሰኔ 16፣ 2010 ዓ.ም. በተደረገው የምስጋናና የመደመር ሰልፍ እንዳልተሳተፈ ያሳያል፡፡

ከ91% እስከ 96% የሚሆነው የአዲስ አበባ ነዋሪ ለምን በሰኔ 16፣ 2010 ዓ.ም. በተደረገው የምስጋናና የመደመር ሰልፍ እንዳልተሳተፈ ለማወቅ በቀጣይ ተጨማሪ ጥናት ለሚያደርጉ በመተው የውሸት ሪፖርቶች Trend ለማሳየት እሞክራለሁ፡፡

## *የውሸት ሪፖርቶች Trend*

በዚህ ስሌት መሰረት ይህ መስቀል አደማባይ መያዝ የሚችለውን ከፍተኛው መጠን 675 ሺ እንደሆነ አሳይቶናል፡፡ ነገር ግን በየጊዜው የመነገሩ ቁጥሮች ከዓመት ዓመት እንደ ዋጋ ንረት እየጨመሩ መጥቷል፡፡ ለምሳሌ ከምርጫ 1997 ዓ.ም ዋዜማ ተነስተን ስናይ

### *የኢህአዴግ የምርጫ ድጋፍ ሰልፍ*

በ1997 ዓ.ም. ኢህአዴግን በመደገፍ በመስቀል አደባባይ ተገኘ ተብሎ በመገናኛ ብዙሃን የተሰራጨው የሰው ብዛት ከ አንድ ሚልዮን በላይ የሚል ነበር፡፡ አሁን በትንታኔ ከተደረሰው መያዝ የሚቻለው ከፍተኛ መጠን (ማለትም 675 ሺ) ሲነፃፀር የ148.2% ዕድገት ያለው ሲሆን ይህም 48.2% ውሸት ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ስለዚህ ኢህአዴግ በጥልቅ ተሃድሶው የገመገመው የውሸት ሪፖርት ከዛ መጀመሩ ያመላክታል፡፡

### *የቅንጅት የምርጫ ድጋፍ ሰልፍ*

በተመሳሳይ መልኩ በ1997 ዓ.ም. ከኢህአዴግን ቀጥሎ ቅንጅትን በመደገፍ በመስቀል አደባባይ ሰልፍ የተደረገ ሲሆን፣ በሰልፉ ተገኘ ተብሎ በመገናኛ ብዙሃን የተሰራጨው የሰው ብዛት ከ ሁለት ሚልዮን በላይ የሚል ነበር፡፡ አሁንም እላይ በትንታኔ ከተደረሰው ከፍተኛ መጠን (ማለትም 675 ሺ) ሲነፃፀር የ296.3% ዕድገት ያለው ሲሆን ይህም የሚያሳየው 196.3% ውሸት ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለለው የኢህአደዴግ ውሸት 48.2% ሲሆን የተቋዋሚ ድርጅቶች (የቅንጅት) ውሸት ደግሞ ለማመን የሚያስቸግር 196.3% ወይም 4 እጥፍ ነበር ብሎ ማደማደም ይቻላል፡፡

### *የጠ/ሚ ዶ/ር አብዩ የምስጋናና የመደመር ሰልፍ*

በተመሳሳይ ዘንድሮ በሰኔ 16፣ 2010 ዓ.ም. ጠቅላይ ሚንስትራችን ዶ/ር አብዩ አሕመድ ለማመስገን በተመሳሳይ ቦታ በመስቀል አደባባይ በተደረገው የምስጋናና የመደመር ሰልፍ፤ በአስተባባሪ ኮሚቴና በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን የተሰራጨው ዜና ሲታይ በሰልፉ ተገኘ የተባለው ብዛት 5-ሚልዮን የሚል ነበር፡፡ አሁንም እላይ በትንታኔ ከተደረሰው ከፍተኛ መጠን (ማለትም 675 ሺ) ሲነፃፀር የ740.74% ዕድገት ያለው ሲሆን ይህም የሚያሳየው 640.74% ውሸት እንደሆነ ነው፡፡

የተቋዋሚ ድርጅቶች (የቅንጅት) ውሸት ደግሞ ለማመን የሚያስቸግር 196.3% ወይም 4 እጥፍ ነበር ብሎ ማደማደም ይቻላል፡፡

ከዚህ መረዳት የሚቻለለው አሁን በዶክተር አብዪ አሕመድ የመመራው ኢህአደዴግ፣ በመደደመር ምክንያት የድሮ ተቋዋሚ የዛሬው ተፎካካሪ ድርጅቶች በሙሉ፣ የትምክህቱ፣ የጠባቡ፣ በውስጥም በውጭም የሚኖሩ በአሸባሪነት የተፈረጁ ድርጅቶች፣ የተለያዩ ሃይማኖት አክራሪዎች፣ የሻብያ ደጋፊዎች፣ በሽብር እና በአክራሪነት ወንጀል ተፈርዶባቸው ታስረው የነበሩና በፍቅርና በይቅርታ የተፈfቱ፣ በተለያዩ ወንጀሎች ታስረው የነበሩና አሁን የተፈቱ ሁሉንም ያጠቃለለ የመደመር ሰልፍ ሲደረግ የውሸቱም መጠን በዛው የዓይነቱ ብዛት ወደላይ አሻቅቧል፡፡ በ1997 ዓ.ም. የነበረው የ48.2% ውሸት አሁን በ13.3 እጥፍ ሲያድግ ከቅንጅቱ ውሸት ጋር ሲነፃፀር ደግሞ በ3.3 እጥፍ ዕድገት አለው፡፡ እንግዲህ መደመር ሲባል በውሸትም መደማመር ማለት ነው፡፡

የውሸት ሪፖርቱከ48.2% ብድግ ብሎ አሁን በመደመር ላይ 640.7% መድረሱ አሁንም ጥልቅ ተሃድሶው ችግሮቹን አውጥቶ ከመናገር ውጭ፣ በተግባር መለወጥ የሌለና ተራ ፕሮፓጋንዳ ብቻ መሆኑ ያሳያል፡፡ ስለዚ ኢህአዴግ አሁንም ወደ ድሮ ቦታው ሊመለስ ከሆነ ወደ ዳግም ጥልቅ ተሃድሶ መግባት አለበት ካልሆነ የጨው እጣ ነው የሚጠብቀው፡፡

*ቸር እንሰንብት*

*ህዳሴ ኢትዮጵያ፣*

*ሰኔ 30፣ 2010 ዓ.ም.*